# መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎችን በነፃ

# እያደሉ ያሉት ተስፋዬ እና ግብረአበሮቹ ናቸው

ዮናስ 10/10/12

የዚህ ጽሁፍ የትኩረት አቅጣጫ ሰሞንኛውን የአገሬ ፖለቲካና በተለይም የኢህአዴግን የመተካካት ሥርዓት ተከትሎ ከውስጥና ከውጭ በተለይም ተስፋዬ ገብረአብ እና ግብረ አበሮቹ በየድረ ገጹ፣ በየመጽሄትና ጋዜጣው በነፃ የሚያድሏቸውን መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎችን ከተጨባጩና በሕዝቡ እውቅና ከተሰጠው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አንፃር የሚፈትሽና የሚያስቃኝ ነው፡፡

የኢህአዴጉን ሊቀመንበርና የአገራችንን ጠቅላይ ሚኒስትር ህልፈተ ህይወት ተከትሎ በኢህአዴግና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ይፈጠራል በሚል ግምት በርካታ የሚርት አጀንዳዎች ተለቀው መሰራጨታቸውና ለስኬቱም ሲባል በርካታ መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎች ታድለው እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሆኖም ሁሉም ነገርና በየደረጃው የተሞከሩት አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ሲከሽፉና ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ሲደረግ በአገሪቱ ሠላምና ልማት የተበሳጩ የሚመስልባቸው እነዚህ ኃይሎች አሁንም ሽግግሩን እና ሥርዓቱን በማብጠልጠልና በሌላ የሁለተኛ ዙር ዘመቻ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው፡፡

ከሽግግሩ በኋላ እንኳን ተስፋዬ ገብረአብ የተባለ ከይሲ "ዣንጥላው ተቀዷል" በሚልና "የኃይለማርያም አንገት" በሚሉ ርዕሶች መርዙን መርጨቱና የመርዙንም ማርከሻ እነሆ ማለቱ ይታወሳል፡፡ ዛሬም ቢሆን ተስፋዬና መሰሎቹ ከበፊቱ ብዙም ያልተለየ ነገር ግን አዲስ የመሰላቸውን ከረሜላ ደግሞ መርዝ በመቀባት በብሎጋቸው ላይ እያቡለገለጉ፤ በድረ ገጻቸው ላይ እየደረገጹ ይገኛሉ። እኔም ማርከሻውን ዛሬም በድጋሜ እነሆ በማለት ርካሽነታቸውን በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፌ አረጋግጣለሁ፡፡ ከተስፋዬ ገብረአብ ጀምሬ በስደተኛው አመፀኛ አቤ ቶክቻው ተሻግሬ ደግሞ ወደ አገሬ በመመለስ ልኩስኩሱን ሀሳባቸውን አልኮሰኩሳለሁ፡፡

ተስፋዬ በባለፈው የ"ኃይለማሪያም አንገት" መጣጥፉ ስለኃይማሪያም አለመቻል ብዙ ከቀደደልን በኋላ የአቶ ኃይለማርያም ደሣለኝ ብቃትና አቅም ትዝ ሲለው እና በኋላ ላይ ያለው ሁሉ ሳይሆን ሲቀር ማፈሩ የማይቀር መሆኑን ሲገነዘብ በመጣጥፉ ማጠቃለያ ላይ

"የኢየሱስ ኃይል አቅም ይሆነዋል" በማለት አጠቃሏል፡፡ እዚህ ላይ ግን አሁንም ቢሆን ስለኃይለማርያም አቅም እጅ ለመስጠት ባለመፈለጉ የኢየሱስ ኃይልም ቢሆን አቅም ሊሆነው እንደሚችል "ሰው ነገረኝ" በማለት ነው የገለፀው፡፡

እኔም በማርከሻ መጣጥፌ ተስፋዬ ሊታመን አይችልም፤ ኋላ ላይ አፍርበታለሁ ብሎ ለሚያስባቸውና ግን ደግሞ ለሴራዬ ይጠቅመኛል ብሎ ላሰባቸው የተፈበረኩ የቃላት ጋጋታዎቹ "እገሌ ነገረኝ" "ከእገሌ ሰማሁ" አንዳንዴም ሌብነት መሆኑን ዘንግቶ "እገሌን ኢንተርቪው ላደርግ ቢሮው ገብቼ ወጣ ሲልልኝ አጀንዳውን ከፍቼ አይቻለሁ" የሚሉ የማጨናበሪያ ቃላት የሚጠቀም ስለመሆኑ በበርካታ ማሣያዎች አብራርቼ እንደነበር

ይታወሣል፡፡ ለአብነት ያህል ከኮሜዲያን ደረጀ ኃይሌ ጋር ለደቂቃ ተገናኝተው ቀርቶ ተያይተው የማይተዋወቁ መሆኑን ደረጀ ለአንድ ባልንጀራዬ ያረጋገጠበትን እና ተስፋዬ ግን "በአንድ ወቅት ከኮሜድያን ደረጀ ጋር ቁጭ ብለን ስናወራ..." ብሎ በጋዜጠኛ ማስታወሻው የተቀደደውን ማስታወሱ በቂ ነው፡፡ <u>እንዳልኩትም</u> ተስፋዬ ለምዶበታልና ከሰሞኑ ባደላቸው መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎቹ አሁንም "አንድ ጓደኛዬ ነገረኝን" አስቀድሟል።

“ስብሃት ነጋ በፓልቶክ ክፍል ተጋብዞ ባደረገው ንግግር "ለኦርቶዶክስ ለአማራ ብቻ ተወስኖ የቆየውን የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥልጣን ለተጨቆነው ሕዝብ አስረከብነው" <u>ማለቱን አንድ ጓደኛዬ ነገረኝ</u>፡፡” የተመሰረተበትን የተስፋዬ ልማድ ልብ ይበሉ፡፡ ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ ግን ይህ አይደለም። ስለ እውነት ለመናገር ለተስፋዬ ስብሀት እንዲህ አለ ብሎ የነገረው እንደሌለ መገመት ይቻላል፡፡ ስብሃት ብሎም እንኳ ቢሆን ፓልቶክን ከሚከታተሉ አንባቢያን ልታረም እችላለሁ፡፡ ስብሃት ብሏል እንኳ ብለን እንውሰድና ተስፋዬ ይህቺን የስብሃት ንግግር ለምን ከሌሎቹ የስብሃት ንግግሮች ለይቶ ለቀቃት? የሚለውን ጥያቄ በትነን እንመልከት፡፡

የተስፋዬ የእብደት መነሻና መንፈሰ ጽርፈት (የስድብ መንፈስ) ወይም የቃላት አረፋ የሆነውን "የቡርቃ ዝምታ" ወደኋላ ተመልሰን እናስታውስ፡፡ በአኖሌ ዋቆና በሃወኒ የወካላቸውን ኦሮሞዎች በነ ... ከወከላቸው አማራዎች ጋር በማናከስ ፌዴራላዊ ስርዓቱን ለማወክና የብሄር ግጭት ለመቀስቀስ እንዲሁም በአማራው ብሄረሰብ ላይ ያለውን ጥላቻ የገለፀበትን መንገድ አንዘነጋም፡፡

ዛሬም ከአማራ ትከሻ ላይ ያልወረደው ተስፋዬ ደግሞ ከወዲያኛውና ከጎረቤቱ ጋር ለማላተም በአቦይ ስብሃት በኩል ከተፍ አለ፡፡ በመሠረቱ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ከጭቆና የተላቀቁት በግንቦት 20 ቀን 1983 እንጂ አሁን አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ የአንድ ግለሰብ ሥልጣን መያዝ ደግሞ በራሱ የሕዝቦችን ከጭቆና መላቀቅ አያመላክትም፡፡ የሥልጣኑ ባለቤቶች ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንጂ የኃይለማርያም የብቻው አይደለም፡፡

ተስፋዬ ግን የዛሬ 21 ዓመት ከጭቆና የተላቀቁትን እና የሥልጣን ባለቤት የሆኑትን የደቡብ ሕዝቦች ዛሬ ደርሶ በስብሃት በኩል ከጭቆና ተላቀቁ ሲል ይቀድልናል፡፡

ተስፋዬ የእፉኝት ልጅ ከይሲ ነው የምላችሁ ወድጄ ወይም ከመሬት ተነስቼ እንዳይመስላችሁ፡፡ ሰውዬው መርዝ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አሁን ያለውን ሁኔታ ያውቀዋል። ከዚያም ጥቂት የአማራ ብሄርተኞች እና ትምክተኛ ኃይሎችንም አሁን ከተደረገው የሥልጣን ሽግግር አንፃር ልብና ኩላሊታቸውን ከልምዱ በመነሳት መመርመሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም መርምሮ ከደረሰበት የግምት ማጠቃለያው ተነሳና በስብሃት በኩል አድርጎ መርዝ የቀባቸውን ከረሜላዎች በነፃ አደለ፡፡ የተስፋዬ እንጭጭነት በዚህ ብቻ ቢያበቃ ጥሩ በነበረ። ግን ይቀጥላል፡፡

ተስፋዬ እዚህችው አገር እየሰራ ሳለ የወጣው ህገ መንግሥትና ኃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውን ስለማረጋገጡ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ኃይለማርያም የሥልጣን ባለቤት የሆነው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦችን

(ደኢህዴንን) ወክሎ በህገ መንግሥቱና በድርጅታዊ ፕሮግራሙ መሠረት እንጂ ፕሮቴስታንትን ወክሎ አይደለም፡፡ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት አማሮችም ቢሆኑ ውክልናቸው ለአማራው ህዝብና ብአዴን እንጂ ለኦርቶዶክስ እንዳልሆነም ይታወቃል፡፡

ይህም ባይሆንና በተስፋዬ ሀሳብ መሠረት ብናንሰለስለው ከየትኛው አማራ ላይ ተነጥቆ ለአቶ ኃይለማርያም መሰጠቱ ግልጽ አይደለም፡፡

እውነቱን ነው የምላችሁ ተስፋዬ ከይሲ ነው፡፡ እርሱ ራሱ እንደሚለው አቦይ ስብሃት ባመኑበት ጉዳይና እርግጠኛ በሆኑበት ጉዳይ ላይ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይከራከራሉ፣ ይጽፋሉ፡፡ ግን ቅድሚያ የሚሰጡት ለሃሳብ እንጂ ለግለሰብ አለመሆኑም መታወቅ አለበት፡፡

በቅርብ ጊዜ አፄ ሚኒልክን በተመለከተ በፍትህ ጋዜጣ ላይ ተከታታይ ጽሁፎችን እና ክርክሮችን ማድረጋቸውን አስታውሳለሁ፡፡ ተከራካሪዎቻቸው ደግሞ መሞገቻ ሃሳባቸው ታሪክና ሀሳብ ሳይሆን የብሄር ጥላቻን መሠረት ያደረገ በምኒልክ  አመካኝቶ የአማራ ብሄር ላይ ያነጣጠረና ሰውዬውን ከአማራ ብሄረሰብ ጋር ለማጋጨት በነፃ የታደሉ መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎች ነበሩ፡፡

ተስፋዬ ገብረአብ ከይሲ ነው፡፡ ይህቺን ከአፄ ምኒልክ ጋር የተያያዘችውን የአቦይ ክርክር አንብቧል። እሱም ቢጠየቅ በፍትህ ጋዜጣ ላይ የተደረገውን ሙግት አንብቤያለሁ ባይል እንኳ “ሰው ነግሮኛል” ማለቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ይህቺኑ ቁንጽልና ውል የለሽ ምልልስ መሠረት በማድረግ ሌሎችንም “ሰው ነገረኝ”ን መነሻ ያደረጉ ግን ተጨባጭ ያልሆኑ ጉዳዮችን በአቦይ አስመስሎ ማስታወስ (የሰውዬውንም የመሰላቸውን ከመናገር ወደ ኋላ ያለመመለስ እውነታ እንደጥሩ ማሳመኛ እድል በመጠቀም) አማራና ትግሬን ለማባላት በተስፋዬ በኩል ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም ሰው ከነገረው የአቦይ የፓልቶክ ንግግር በመለስ ወደ ምርጫ 97 ይሻገራል፡፡ የአቦይ ስብሃት ንግግሮች ለተስፋዬ በርካታ ቢሆኑም ዝነኛ ግን አይደሉም። ዝነኛ አይደሉም ያለው ደግሞ ያለምክንያት እንዳይመስላችሁ፤ ከረሜላዎቹ ከተቀቡት መርዞች ውስጥ አንዱ ይህ ዝነኛ አይደሉም የሚለው ሐረግ ነው፡፡

“ስብሃት ነጋ በርካታ ዝነኛ ያልሆኑ አባባሎች አሉት፡፡ ለመጥቀስ ያህልም፤ "…ትግሬዎችን ወደመጡበት እንመልሳቸዋለን” የተባለችው የበድሩ አደም ነጠላ ዜማ የተለቀቀች ሰሞን፣ ስብሃት እንዲህ ሲል መልስ ሰጥቷል፣ “…እኛ ወደመጣንበት ስንባረር፣ መንዜዎችን ሰሜን ሸዋ አራግፈን ነው የምናልፈው!” ይህን አቦይ ስብሃት ተናገሩትም አልተናገሩትም ተስፋዬ ዝነኛ ንግግር አይደለም ያለበት ምክንያት ለአማራው ተጨንቆ ሳይሆን ጥገኛው አማራ መርዟ ላይ እንዲያሰምርባት በመፈለግ ነው፡፡ ይህንኑም ፍላጎት ተስፋዬ ራሱ ወረድ ብሎ “…ዳሩ ግን ከብሽሽቁና ከእልሁ በስተጀርባ ያለው ፖለቲካዊ ይዘት ከቶ ምንድነው?" ሲል በጥያቄ አስመስሎ ያረጋግጣል፡፡

የብሄር ጉዳይ ቢያንስ ህገ መንግሥታዊ ድጋፍም ያለው በመሆኑ ለማስመሰልና ለማምታታት ስለሚመች ተስፋዬ ከረሜላዎቹን ይህንኑ የብሄር መርዝ እየቀባ ቢቀጥልም  አላዋጣውም። መጽሃፍም ጻፈ፤

በማስታወሻውም አለው፤ ግን ጠብ የሚል ነገር አጣ፡፡ ስለሆነም አሁን ቡኮውን ወደ ኃይማኖትና እምነት በመመለስ ማላቆጡን ጀምሯል፡፡

ቀደም ብዬ እንዳልኩት የመንግሥት ባለሥልጣናት ውክልና የሕዝባቸውና የመሪ ድርጅታቸው ነው፡፡ መንግሥትና ኃይማኖትም የተለያዩ ስለመሆናቸው በህገ መንግሥቱ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የኃይለማርያም ውክልናም የፕሮቴስታንት ሳይሆን የሕዝቡና የደኢህዴን/ኢህአዴግ ስለመሆኑ ፊደል የቆጠረው ዜጋ ቀርቶ ወረቀት ገልጦ የማያውቀው ሁሉ ያውቀዋል፡፡ ስለሆነም አክራሪነት በሁሉም ቦታና ኃይማኖቶች ውስጥ መኖሩን የሚገነዘበው ከይሲ የከሬሜላዎቹን መርዝ ወደ እምነት አዙሮታል፡፡

“የስብሃትን አባባል ተከትሎ ለኃይለማርያም “ፀረ ማርያም” እና “ፀረ አማራ” የተባሉ ቅጽሎች እየተሰጡት ነው፡፡” ተስፋዬ ምኞቱን ሆኗል ብሎ የሚናገርና በስድብ መንፈስ የተለከፈ መሆኑን በዚህችውና ከላይ ቀንጭቤ ካቀረብኳት የ"ፀረ አማራ" እና "ፀረ ማርያም" ብሂሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የኃይለማርያምን ብቃት፣ (የግሉ) ኃይማኖታዊ ስብዕና፣ ድርጅታዊ ቁመናና የአመራር ጥበብ እንዲሁም ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን እና የደኢህዴን ድርጅታዊ ወዝ ትተን እንኳን የተስፋዬን ቁንጽል ሀሳብ እንደወረደ እንመዝነው ብንል፦ ኃይለማርያም ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆነ ገና ስንት ቀን ሆኖት ነው የፀረ አማራና የፀረ ማርያም ምልክቶች የታዩበት? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት የተስፋዬን ቁንጽልነትና የበሬ ወለደ "ሰው ነገረኝ" "ድረ ገጽ አሳየኝ" ትንተና መገንዘብ ይቻለናል፡፡

ከተስፋዬ "ጋዜጠኝነት" እና "ደራሲነት" የሚብሰው ጉደኛነቱ ነው፡፡ ጉዱ ተዘብዝቦ አያልቅም፡፡ መርዙም የከይሲው እፉኝት ዓይነት ነው፡፡ አሁንም ከአማራ ትከሻ ላይ እንደ መዥገር ተጣብቋል፡፡ “በእግረ መንገድ ምክትሉ ደመቀ መኮንን እሥላም መሆኑ እየተጠቀሰ “የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሸጠ” የሚል ካባ ይመረቅለታል፡፡" ይላል የተስፋዬ መጣጥፍ። ለደመቀ ካባውን የደረበው ግን ባለፈው መርዘኛ መጣጥፉ ራሱ ተስፋዬ ነው። በትምህርተ ጥቅስ ሊሸውደን "ይመረቅለታል" ብሎ እጥፍ ይላል፡፡

ተስፋዬ የገዛ የራሱን መጣጥፍ ባለቤት ይነሳዋል፡፡ “ባለቤት አልባው መጣጥፍ እንደሚጠቁመው ኃይለማርያም ወደፊት “በፀረ አማራነት አቋሙ” ሊገፉበት ይችላል? ለመሆኑ እንዲህ ያሉ ያልተረጋገጡ መረጃዎችን የሚለቀው ማነው? ለምን ዓላማ? በእርግጥ ኃይለማርያም ፀረ አማራ አቋም አለው? ፅሁፎቹ፣ “ትምክህተኞች” በግዴለሽነት የሚበትኗቸው ናቸው ወይስ ህወኃት ሆን ብሎ ለዓላማው የሚያሰራጨው? መረጃ ስለሌለኝ አላውቅም።” ሲል እንደ እስስት ተቀይሮ ከጨዋታው ሊወጣ ይሞክራል፡፡ ግን ተስፋዬ መረጃ አለው፡፡ ጽሁፉን የሚለቀው “ትምክህተኛው” እና “ህወኃት” እንዳልሆኑም ልቡ ያውቃል፡፡ የጽሁፎቹ (የከረሜላዎቹ) ባለቤቶች ተስፋዬ እና ግብረ አበሮቹ ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ብሂር ተኮርና እምነት ተኮር መርዞች የ“ትምክህተኛው” እና የ"ህወኃት" ሳይሆን የተስፋዬና መሰሎቹ እርስቶች ናቸው፡፡ አብረዋቸው ተወልደው አድገዋል፡፡

ከሁሉም ያስገረመችኝ ግን በእነዚህ መርዝ የተቀቡና በነፃ የሚታደሉቱ ከረሜላዎች ተጠቃሚ መሆን የሚመኘውና ያሰበው ተስፋዬ መሆኑን የፅሁፉ አወራረድ ስለሚያመላክት ሌላ ማጠፊያ ማበጀት እንዳለበት

የተገነዘበው ተስፋዬ “መረጃ ስለሌኝ አላውቅም” ከምትለው ሽፍጡ በመለጠቅ “ይህን በመሰሉ ቅስቀሳዎች ግን ወያኔ ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ማሳመን ይቻላል” በማለት ለማምለጥ ይሞክራል፡፡

ተስፋዬ “በኃይለማርያም አንገት” መጣጥፉ የኃይለማርያምን "አይችልም" ከመስበክ ጀምሮ "ኢየሱስ ኃይል ይሆነዋል" እስከሚለው የ"ሰው ነገረኝ" መላምቱ ዘልቆ ወንበሩ የምኒልክና ቀይ መሆኑን አስታውሶ "ወንበሩ ይበላዋል" የሚል ድምዳሜ ላይ እንዳላደረሰው ሁሉ ለዛሬው መጣጥፉ ኃይለማርያምን በጥቂቱም ቢሆን ማሞካሸት ዓላማዬን ለማሳካት ይጠቅመኛል በሚል ግምት በኃይለማርያም አንገት ላይ የጠመጠመውን ገመድ አላልቶታል፡፡

ዓላማው ህወኃትን የአማራ ጠላት ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም በኃይለማርያም በኩል እግቱን መለኮስ ጠቃሚ ነው ብሎ አምኖበታልና እንዲህ ይላል፦ “ያነበበ፣ በማንበብ ላይ ያለና የተማረ ሰው ነው፡፡ የተማረና ያነበበ መሆኑ፣ ብቁ የፖለቲካ መሪ ሊያደርገው ባይችልም፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቢሮ ሲለማመደው አንጎሉን መጠቀም ሊጀምር ይችላል፡፡ ብለው ይሰጋሉ፡፡ ከኃይለማርያም በኩል ያጋጥመናል ብለው ከሚሰጉት ነገር ዋናው፣ ከብአዴን ወይም ከታቃዋሚዎች፣ በተለይ (ከአማራ ተቃዋሚዎች) ጋር የዓላማ አንድነት ከመሠረተ ህወኃትን ማንሳፈፍ የመቻሉ እውነት ነው፡፡”

ተስፋዬ በእርግጥም አብዲል ወይም የቅናት ዛር ተነስቶበታል፡፡ ምክንያቱም ህወኃት፣ ብአዴን፣ ደኢህዴን፣ ኦህዴድ (ኢህአዴግ) እንዲህ ተስፋዬ እንደሚተረተርልን "የመንደር ህፃናት" ክምችት እንዳልሆኑ ጠንቅቆ ያውቃቸዋል፡፡ እንደ ተቋም ሰፊ መዋቅር ያላቸው፤ የበሰሉና በተግባር የተፈተኑ ከኢትዮጵያ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናና የይችላሉን "አዋርድ" የተቸሩ ስለመሆናቸውም ያውቃል፡፡ ታዲያ ይህን እያወቀ እኛም የኢህአዴግን ድርጅታዊና መንግሥታዊ አቅም በተግባር እያየን እንደ ህፃናት የሰፈር ፀብ ስለ ህወኃት እና ብአዴን፤ ደኢህዴን እና ኦህዴድ መተርተሩ ከምን የመነጨ ነው? ወይ ቅናት ነው ወይም እብደት ካልሆነ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡

አቶ ተስፋዬ እብድ ነው፡፡ ከላይ ከመጣጥፉ ላይ እንደገለጽኩላችሁ “መረጃ የለኝም አላውቅም” እንዳላለ፤ “ባለቤት አልባው መጣጥፍ” እንደሚለው ብሎ እንዳልታጠፈ፤ በጽሁፉ ማጠቃለያ ላይ የጽሁፎቹ ባለቤት ራሱ ስለመሆኑና መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎቹን በቀጣይነትም በነፃ የሚያድል እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡

“እንግዲህ ብዕሮች ኃይለማርያም ላይ ማነጣጠራቸው ግድ ነው፡፡ ኃይለማርያምን ከፀረ ማርያምነት እስከ ፀረ አማራነት ፈርጀነዋል፡፡ ከአሻንጉሊትነት እስከ አምባገነንነት መድበነዋል። ከየዋህነቱ እስከ መሰሪነቱ ልቡን ቆፍረን ተንትነናል፡፡ ከጭንቀታምነቱ እስከ ኮስታራነቱ እንደ ሞተር በትነን ገጥመነዋል…።"

የተሰመረባቸውን ቃላት ልብ በሉልኛማ “ፈርጅነዋል፣” “መድበነዋል”፣ “ተንትነናል”፣ “ገጥመነዋል” ። ተስፋዬ ጽሁፎቹን "ትምክህተኛው" ወይም "ህወኃት" ነው የሚበትናቸው ቢልም ከላይ በተሰመረባቸው ቃላት መሠረት የጽሁፎቹ (መርዝ የተቀቡ ከረሜላዎቹ) ባለቤት ተስፋዬና ግብረ አበሮቹ ስለመሆናቸው ከዚህ በላይ አስረጂ ከወዴት እናምጣ? በዚሁ መሠረት፦

እኔም የተስፋዬን ኳዶችና መርዝ የተቀቡ ከረሜላ አዳዮች ከሆኑት ውስጥ አቤ ቶክቻውን አነሳለሁ፤ የኢህአዴግንም ነባራዊ ሁኔታና ኢትዮጵያን እቃኛለሁ፡፡ ግን ፋታ ያስፈልገናልና አረፍ  እንበል እና በክፍል 2 መጣጥፌ እንገናኝ፡፡